| | |
|---|---|
| **ሁሉም የሥራ ቦታዎች ለቪክቶሪያ መንግሥት ኩውአር ኮድ/QR Code አገልግሎት (ከአንዳንድ የተወሰኑ ካልሆነ) በአገልግሎት ቪክቶሪያ አፕ/app. አድርገው ይጠቀማሉ።**<br>**አንድ ጎብኚ/እንግዳ ለመግቢያ ማጣሪያ በራሱ ማካሄድ ካልቻለ፤ የአገልግሎት ቪክቶሪያ መመዝገቢያ ማጣሪያ አገልግሎት በኩል ወደ መገልገያ ቦታና ወደ ንግድ ስራ ቦታው ለመግባት የራሳቸውን ስማርት ስልክ፣ ታብለት ወይም ኮምፑተር ለመጠቀም ይፈቅድላቸዋል።**<br>**ይህን ለመጠቀም ነጻ፤ ፈጣንና ቀላል ነው።** | **ለቪክቶሪያ መንግሥት ኩውአር ኮድ/QR Code አገልግሎት ለመመዝገብ ድረገጽ፤coronavirus. vic.gov.au/register-to-use-vic-gov-qr-code-service**<br>**ወረርሽኝ ካለ፤ የቫይረሱን ስርጭት ለማቆም ግንኙነት ላደረጉ ፍለጋ ይህ በፍጥነትና በጥሩ ሁኔታ መርዳት የሚያስችል ነው።**<br>**ሰራተኞች፤ ደንበኞችና ጎብኝዎች የመግቢያ ማጣሪያ ማካሄዳቸውን ማረጋገጥ ነው።** |

## በተቀራረቡ ቦታዎች ላይ ግንኙት ማድረግን ማስወገድ

| ማድረግ ያለብን እና የተሰጠ ምክር | እርምጃ |
|---|---|
| በተቀራረበ ቦታዎች ላይ ለሚሰሩ ሰራተኞች የሚያጠፉትን ጊዜ መጠን መቀነስ አለባቸው። ይህን ማድረግ የሚችሉት:<br>• በውጭ አካባቢ ሆኖ መሥራት የሚችሉ ሲሆን ነው።<br>• በተቻለ በብዛት በውጭ ባለ እንቅስቃሴ ሥራ ላይ በመንቀሳቀስ፤ ይህም ለደንበኞች አገልግሎት መስጠት፤ ለስብሰባዎች፤ ለሻሂ/ቡና ክፍሎች፤ ለምሳ እረፍትና ለተዘጉ ክፍሎች ያካትታል።<br>• መስኮቶችንና በሮችን በመክፈት አየር እንዲቀሳቀስ በማድረግ ነው።<br>• የንጹህ አየር እንቅስቃሴን እንዲባዛ ማድረግ። | በሮችን ወይም መስኮቶችን መክፈት ወይም በውጭ በሚካሄዱት መቀየር ይችላሉን? |

## የሰራተኞች መጥለቅለቅ

| ማድረግ ያለብን እና የተሰጠ ምክር | እርምጃ |
|---|---|
| በአንድ የሥራ ቦታ ላይ በተመሳሳይ ፈረቃ ሥራ ያሉትን የሰራተኞች ቡድን ምደባ ግምት ውስጥ ማስገባት። ተግባራዊ ከሆነ የፈረቃ ሥራ በሚቀየርበት ጊዜ እላፊ የሆኑትን ሰራተኛ ለማስወገድ መሞከር። | መገናኘት ለሚችሉት የሰዎች ቁጥርን ለመቀነስ፤ ያሉትን ሰራተኞች በቡድን ያስቀምጣሉን?<br>ወረርሽኝ ካለ፤ በሞላው የርስዎ ቡድኖች መሰራጨትን እንዴት ማቆም ይችላሉ?<br>ቡድኖች የሚመደቡት በተለያዩ ቀናት ነውን? |

ጥቃቅን የንግድ ሥራዎች እንዴት ለኮቪድ ጥንቃቄ/COVIDSafe እቅድ እንደሚፈጥሩ በዚህ ሰነድ መመሪያ ይረዳቸዋል።
እባክዎ ለእርስዎ ኢንዱስትሪ ወቅታዊ አስፈላጊ የሆኑትን ለማረጋገጥ በድረገጽ: **CORONAVIRUS.vic.gov.au** ላይ ማየት።

ባለን የግላዊነት ፖሊሲ መሰረት ላቀረቡት ማንኛውም መረጃ በሚስጢር እንደሚያዝ እና ለተጠቀሰው ጉዳይ ብቻ ይጠቅማል።

ስለ የእኛ ግላዊነት ፖሊሲ ለበለጠ መረጃ እባክዎ በኢሜል **icc@ecodev.vic.gov.au** ወይም ለንግድ ሥራ ቪክቶሪያ/Business Victoria ሆትላይን መስመር በስልክ 13 22 15 ይደውሉ።

**የመግቢያ ማጣሪያ በእያንዳንዱ ቦታ ሁልጊዜ**

ከርስዎ ኮቪድ ጥንቃቄ/COVIDSafe እቅድ ጋር በተዛመደ እርዳታ በድረገጽ፡ **CORONAVIRUS.vic.gov.au** ገብቶ ማየት ወይም ለንግድ ሥራ ቪክቶሪያ/ Business Victoria ሆትላይን መስመር በስልክ **13 22 15** መደወል። ተርጓሚዎች ይቀርባሉ።

DJPR 13413

የመግቢያ ማጣሪያ
በእያንዳንዱ
ቦታ ሁልጊዜ

# የርስዎ ኮቪድ ጥንቃቄ/ COVIDSAFE እቅድ

## 1. ለኮቪድ ጥንቃቄ/COVIDSafe እቅድ አለዎትን?

በቦታው ላይ ለሚሰራ የእያንዳንዱ ንግድ ሥራ ቦታ ለኮቪድ ጥንቃቄ/COVIDSafe እቅድ መኖር አለበት። በሞላው ቪክቶሪያ በሥራ ደህንነትና ስልጣን ባላቸው ሀላፊዎች የማጣሪያ ፍተሻ ይካሄዳል።

## 2. በርስዎ ቦታ ክፍል ላይ ስለወጣው የኮቪድ ጥንቃቄ/COVIDSafe ያውቃሉን?

ለእያንዳንዱ የሥራ ክፍል መመሪያዎች በድረገጽ: **coronavirus.vic.gov.au/guidance-sectors** ላይ ይገኛል። በእያንዳንዱ የሥራ ክፍል መመሪያ ገጽ ላይ ምክርና በተደጋጋሚ ለሚጠየቁ ጥያቄዎች መልሶችን ያካትታል።

## 3. ለርስዎ ንግድ ሥራ የኮቪድ ይንቃቄ/COVIDSafe እንዲኖረው ምን አድርገዋል?

በእነዚህ እርምጃዎች ላይ ለሰራተኞች የግላዊ መከላከያ መሳሪያዎችን በማቅረብ እንደ ጭምብል፤ በርስዎ ንግድ ሥራ ቦታ ላይ ለሚገባ እያንዳንዱ ሰው የመግቢያ ማጣሪያን እንዲያካሂድ፤ የመጸዳጃ/ሳኒታይዘርን ማቅረብ እና በተደጋጋሚ የሚነካኩትን ስፍራዎች በተደጋጋሚ በጸረ-ነብሳት ማጽዳት ያሉትን ያካትታል።

## 4. የርስዎን ኮቪድ ጥንቃቄ/COVIDSafe እቅድ ወቅታዊ ለማድረግ የማን ሃላፊነት ነው?

የርስዎ ኮቪድ ጥንቃቄ/COVIDSafe እቅድ በተደጋጋሚ ግምገማ መደረግ እንዳለበት እና ለእርስዎ ሰራተኞችና ደንበኞች ቅድመ ሁኔታን ለማሟላት አዲስ የወጡትን እገዳዎች እንዲከተሉ ለመርዳት ነው።

## 5. ስለርስዎ ኮቪድ ጥንቃቄ/COVIDSafe እቅድ ሰራተኞችዎ ያውቃሉን?

ስለርስዎ ኮቪድ ጥንቃቄ/COVIDSafe እቅድና ለወሰዱት እርምጃ የርስዎ ሰራተኞች ማወቁ ጠቃሚ ነው። ይህን ማሳወቁ የሚረዳው ለንግድ ሥራዎ ደህንነት የተጠበቀና ከታመሙ እቤትዎ መቆየት ጠቃሚ ስለመሆኑ ይረዳቸዋል። በኮቪድ/COVID-19 በሽታ ምልክቶች የሚካተት ትኩሳት፤ ብርድ ብርድ ማለት፤ መሳል፤ የጉሮሮ ህመም፤ የትንፋሽ እጥረት፤ በአፍንጫ ፈሳሽ ወይም የማሽተት ስሜት ማጣት ይሆናል።

## 6. የርስዎ ኪውአር ኮድ/QR Code አለዎትን?

ሁሉም የንግድ ሥራዎች ለቪክቶሪያ መንግሥት ኪውአር ኮድ/QR Code አገልግሎትን መጠቀም እንዳለባቸው (ከአንዳንድ የተወሰኑ ነጻ መሆን) ታዲያ በእያንዳንዱ ቦታና ጊዜ ለደንበኞችና ሰራተኞች ማስገቢያ ማጣሪያ እንዳሉ ማረገገጥ – ከህንጻው ምን ያህል እርቀት ቢሆኑም ለማረጋገጥ ይሆናል። ይህ ነጻ፤ ለመጠቀም ቀላል እና ለኮቪድ/COVID-19 ስርጭት ለማስቆም ይረዳል። ለመመዝገብ በድረገጽ: coronavirus.vic.gov.au/QRcode ላይ መግባት።

## 7. ደንበኞች ትክክለኛውን እንዲፈጽሙ ተጨማሪ ምልክቶችና የሚለጠፍ ማስታወቂያ ይፈልጋሉን?

ለርስዎ ንግድ ሥራ ምልክቶች፤ ማስታወቂያና ለሚለጠፉት የሚቀርቡት በድረገጽ **coronavirus.vic.gov.au/signs-posters-and-templates**

## 8. በሌላ ቋንቋ መረጃ ማግኘት ይፈልጋሉን?

ለንግድ ሥራ ከኮቪድ ጥንቃቄ/COVIDSafe እቅድ አወጣጥ በተመለከተ መረጃ በተለያዩ ቋንቋዎች በንግድ ሥራ ቪክቶሪያ ሆትላይን መስመር ስልክ 13 22 15 አድርጎ በመደወል እና በድረገጽ:coronavirus.vic.gov.au/translated-information-about-coronavirus-covid-19 ላይ ይቀርባል።

**ለርስዎ ኮቪድ/COVID-19 ክትባት ቀጠሮ ለማቀናጀት በድረገጽ: www.coronavirus. vic.gov.au/vaccine ላይ ይቀርባል።**

VICTORIA State Government

# ሰራተኞችዎና ደንበኞችዎ ደህንነት መጠበቅ የሚችሉት በዚህ ምልኩ ነው።

| | | | |
|---|---|---|---|
| **የንግድ ሥራ ስም:** | | | |
| **አድራሻ:** | | | |
| **እቅዱ የተጠናቀቀበት:** | | **የሥራው አርእስት:** | |
| **የተገመገመበት ቀን:** | | **ቀጣዩ ግምገማ:** | |

## የአካል እርቀትን ተግባራዊ ማድረግ

| ማድረግ ያለብን እና የተሰጠ ምክር | እርምጃ |
|---|---|
| ጠቃሚ ለሆነ የርቀት መጠን ጥንቃቄን ተግባራዊ ማድረግ አለብዎት። በእያንዳንዱ አካባቢ ደህንነቱ በተጠበቀ ምን ያህል ሰዎች መሆን እንደሚቻል በርስዎ ክፍል ባለው መመሪያ ላይ ማጣራት። ለምሳሌ፡ በርስዎ ሱቅ ስፋት 30m$^2$ ሜትር ስኳር ከሆነ፤ በሁለት ስኳር ሜትር ክልል ውስጥ ሁለት ሰዎች ደንብ መሰረት 15 ሰዎች ሊገኙ ይችላሉ። | በርስዎ የሥራ ክፍል ቦታ ላይ ምን ያህል ለብዛትና እርቀት መጠን ማስጠንቀቂያ አለው?<br><br>ለመጠን እርቀት ማስጠንቀቂያ ተግባራዊ ለማድረግ ምን ያደርጋሉ?<br><br>በመግቢያው ላይ ምልክት አስቀምጠዋልን?<br><br>የርስዎን ብዛትና እርቀት መጠን ማስጠንቀቂያ ካልቀጠሉበት ለማረጋገጥ ማነው ሃላፊነት የሚወስደው? |
| ሰራተኞችና ጎብኝዎች በተቻለ መጠን የአካል እርቀታቸውን በ1.5 ሜትር መጠበቅ ዓላማ ማድረግ። | በሥራ ቦታ መግቢያ፤ ሲንቀሳቀሱና በሚወጡበት ጊዜ ያለውን ብዛት መጠን ስብስብ መቀነስ ይፈልጋሉን?<br><br>ሰዎች ተራርቀው በ1.5 ሜትር ለመቆየት ምልክትን በወለል ምልክት ወይንስ በሚለጠፍ እንዲሆን ይመርጣሉ? |
| ስለ በአካል እርቀትን መጠበቅ ለሰራተኞች ማሰልጠን አለብዎት። በዚህ ውስጥ ወቅታዊ ለሆነ የኮቪድ ጥንቃቄን/ COVIDSafe ቅንጅት መረዳትን ያካተተ መሆን አለበት። ይህን ማግኘት የሚቻለው ድረገጽ፡ **coronavirus.vic.gov.au** | የርስዎ ሰራተኞች ስለ አካል እርቀት መጠበቅ ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ እንደተረዳቸው ለማረጋገጥ ምን አድርገዋል? |

## የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ጭምብል ማጥለቅ

| ማድረግ ያለብን እና የተሰጠ ምክር | እርምጃ |
|---|---|
| ሁሉም ሰራተኞች ወቅታዊ በሆነ የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ጭምብል እንደሚያስፈልግ ማረጋገጥ **አለብዎት፡** ዝርዝር መረጃው በድረገጽ፡ **coronavirus.vic.gov.au/face-masks**<br><br>አስፈላጊነቶች በየጊዜው ሊቀያየሩ ይችሉ ይሆናል። | በሰራተኞችዎ የሥራ ክፍል ላይ የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ እንደሚያስፈልግ ተረድቷቸዋልን?<br><br>ለርስዎ ሰራተኞች የሚሆን የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ጭምብሎችን ያቀርባሉን? |

| | |
|---|---|
| እንዴት በትክክል እንደሚገጠም፤ እንደሚጠቀምና በግላዊ መከላከያ ለተጠቀሙበት መሳሪያ (PPE) ወደ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ እንደሚጣል ስልጠናና መረጃ መስጠት አለብዎት።<br><br>እንደገና የሚጠቀሙበት የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ጭምብሎት ከተጠቀሙበት በኋላ በየቀኑ መታጠብ እንዳለበት ለሰራተኞች ምንገር አለብዎት። ይሁን እንጂ በቀን በሚጠቀሙበት ጊዜ የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ጭምብል ከቆሸሸ ወይም ከረጠበ ወዲያውኑ ንጹህ በሆነ የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ጭምብል መተካት አለበት። | የርስዎ ሰራተኞች እንዴት ለግላዊ መሳሪያ PPE መጠቀም እንዳለባቸው እንደተረዱ ለማረጋገጥ የማን ሃላፊነት ነው? |

## ጥሩ ንጽህና ሃይጂን ማካሄድ

| ማድረግ ያለብን እና የተሰጠ ምክር | እርምጃ |
|---|---|
| ብዙጊዚው በጋራ የሚጠቀሙትን ለማጽዳትና በጸረ-ነብሳት ለመጥረግ መሞከር **አለብዎት።** ይህም ብዙጊዜ በተደጋጋሚ የሚነካን ስፍራዎች እንደ የበር እጀታና ተለፎኖችን ያካትታል።<br><br>ማድረግ ያለብዎት:<br><br>• በተደጋጋሚ የሚነካን ስፍራዎች በትክክለኛ የማጽጃና ጸረ-ንብሳት ማጥፊያን ባካተተ ውጤት አድርጎ ማጽዳት<br><br>• በሥራ መቀያየሪያ ጊዜ ማጽዳት ይሆናል። | በተደጋጋሚ የሚነካን ስፍራዎች፤ የበር እጀታን፤ የእንግዳ ማስተናገጃንና የእጅ መደገፊያን ያካተተ በቀን ሁለት ጊዜ በጸረ-ነብሳት ያጸዳሉን?<br><br>በሥራ መቀያየሪያ መካከል ባለው ጊዜ ማጽዳት የማን ሃላፊነት ነው? |
| በጋራ በሚጠቀሙበት ስፍራ ላይ የጽዳት ማካሄጃ ምልክት ማስቀመጥ አለብዎት። | የርስዎ ማጽጃ ማካሄጃ ምልክት የት ነው ያለው? |
| ለሁሉም ሰራተኞች የሚሆን ሳሙና እና የእጅ ማጽጃ/ሳኒታይዘር ማቅረብ እንዳለብዎትና በተደጋጋሚ እጅን እንዲታተቡ ማበረታታት አለብዎት። | በሁሉም መታጠቢያ ጣቢያዎች ላይ ሳሙና እና ውሃ አለዎትን?<br><br>ደንበኞች፤ እቃ የሚያደርሱ ሰዎች፤ ኮንትራክተሮች እና ሰራተኞች በሙሉ በሚደርሱበት ጊዜ ለሚጠቀሙበት ማጽጃ/ሳኒታይዘር ማግኘት ይችላሉን? |

## ሰራተኞች ከታመሙ በፍጥነት መመዝገብና እርምጃ መውሰድ

| ማድረግ ያለብን እና የተሰጠ ምክር | እርምጃ |
|---|---|
| ሰራተኞችዎ ከታመሙ፤ ምንም እንኳን መለስተኛ የበሽታ ምልክት ቢሆንም ምርመራ እንዲያደርጉና እቤት እንዲቆዩ ሰራተኞችን መርዳት **አለብዎት**። | የኮቪድ/COVID-19 በሽታ ምልክቶችን ያውቃሉን?<br><br>አንድ ሰራተኛ የበሽታ ምልክቶች ካለበት፤ እቤት መቆየትና ምርመራ ማካሄድ እንዳለባቸው ያውቃሉን? |
| ማንኛውንም ወረርሽኝ ለመቆጣጠር በሥራው ላይ በድንገት ሊፈጠር የሚችል እቅድ ማውጣት **አለብዎት**። በዚህ እቅድ የሚካተት:<br><br>• ሰራተኛው ቫይረስ እንዳለበት ወይም በሥራ ላይ እያለ በቅርበት ግንኙነት አድርጎ ከሆነ በማሳወቅ የምላሽ እቅድ ማውጣት።<br><br>• የቫይረስ ጉዳይ ባለበት ለሚደረግ ድርጊት የሥራ ቦታን (ወይ በከፊሉ) ለማጽዳት እቅድ ማውጣት።<br><br>• በሥራ ቦታዎ ላይ በኮቪድ/COVID-19 የተያዘ ሰው ካለዎት ለጤና ጥበቃ መምሪያ የቪክቶሪያ ኮቪድ ጥንቃቄ/COVIDSafe እቅድ ለማነጋገር በስልክ 13 23 60 መደወል።<br><br>• ምናልባት በጤና ጥበቃ መምሪያ/Department of Health በኩል ቅርበት ካለ ከተነገሩ እቅድ ማውጣት።<br><br>• ለሥራ ቦታ እንደገና ለመክፈት በጤና ጥበቃ መምሪያ/Department of Health በኩል ተቀባይነት ሲያገኝ እቅድ ማውጣት። | በቦታው ላይ ያሉትን ሁሉንም ሰራተኞችና ኮንትራክተሮች እንዴት መመዝገብ ይችላሉ?<br><br>የርስዎ ሰራተኞችና አቅራቢዎች በሙሉ ተገልሎ መቆያና ምርመራ ማድረግ ካለባቸው፤ እንዴት በፍጥነት ማነጋገር ይችላሉ?<br><br>በሥራ ቦታ ላይ ኮቪድ ከተግኘብዎት፤ ለጤና ጥበቃ መምሪያ/Department of Health እና ዎርክሳፍ/WorkSafe ማን ነው የሚደውል? |